በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን።

# የሕይወት ቀውስ - መደበት- የልብ ሐዘን

## *ክፍል ሦስትና አራት*


## መምህር፡ ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon@gmail.com


***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

## ግንቦት ፳፮ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.

# የሕይወት ቀውስ - መደበት- የልብ ሐዘን በተግባራዊ ዘዴዎች ሲፈተሽ

*ቅዱስ ጳውሎስ*

- #በእስያ ስለ ደረሰብን መከራችን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ታውቁ ዘንድ እንወዳለንና፤ ስለ ሕይወታችን እንኳ ተስፋ እስክንቆርጥ ድረስ ከዓቅማችን በላይ ያለ ልክ ከብዶብን ነበር፡፡; *2ኛ ቆሮ 1፡8፡፡*

*ነቢዩ ዮናስ*

- #አሁንም፥ አቤቱ፥ ከሕይወት ሞት ይሻለኛልና እባክህ፥ ነፍሴን ከእኔ ውሰድ አለው፡፡ … ከሕይወት ሞት ይሻለኛል አለ፡፡ … እግዚአብሔርም ዮናስን፦ በውኑ ስለዚች ቅል ትቈጣ ዘንድ ይገባሃልን? አለው፡፡ እርሱም፦ እስከ ሞት ድረስ እቈጣ ዘንድ ይገባኛል አለ፡፡; *ዮናስ 4፡3፣ 4፡8-9*

*ጌታችን በመዋዕለ ሥጋዌው*

- #ጴጥሮስንም ሁለቱንም የዘብዴዎስን ልጆች ወስዶ ሊያዝን ሊተክዝም ጀመር፡፡ ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዘነች፤ በዚህ ቆዩ ከእኔም ጋር ትጉ አላቸው፡፡;*ማቴ 26፡36-37፡፡*

*ነቢዩ ኤልያስ*

#አክዓብም ኤልያስ ይህን ሁሉ እንዳደረገ፥ ነቢያትንም ሁሉ በሰይፍ እንደ ገደለ ለኤልዛቤል ነገራት፡፡ ኤልዛቤልም፡፡ ነገ በዚህ ጊዜ ነፍስህን ከእነዚህ እንደ አንዲቱ ነፍስ ባላደርጋት፥ አማልክት ይህን ያድርጉብኝ ይህንም ይጨምሩብኝ ብላ ወደ ኤልያስ መልእክተኛ ላከች፡፡ ኤልያስም ፈርቶ ተነሣ፥ ነፍሱንም ሊያድን ሄደ፥ በይሁዳም ወዳለው ወደ ቤርሳቤህ መጥቶ ብላቴናውን በዚያ ተወ፡፡… ; *1ኛ ነገሥት 19፡1-3፡፡*

# የቀጠለ…

- #… እርሱም አንድ ቀን የሚያህል መንገድ በምድረ በዳ ሄደ መጥቶም ከክትክታ ዛፍ በታች ተቀመጠና። ይበቃኛል አሁንም፥ አቤቱ፥ እኔ ከአባቶቼ አልበልጥምና ነፍሴን ውሰድ ብሎ እንዲሞት ለመነ። በክትክታውም ዛፍ በታች ተጋደመ እንቅልፍም አንቀላፋ እነሆም፥ መልአክ ዳሰሰውና። ተነሥተህ ብላ አለው። ሲመለከትም፥ እነሆ፥ በራሱ አጠገብ የተጋገረ እንጎቻና በማሰሮ ውኃ አገኘ። በላም ጠጣም፥ ተመልሶም ተኛ። የእግዚአብሔር መልአክ ደግሞ ሁለተኛ ጊዜ መጥቶ ዳሰሰውና። የምትሄድበት መንገድ ሩቅ ነውና ተነሥተህ ብላ አለው። ተነሥቶም በላ ጠጣም በዚያም ምግብ ኃይል እስከ እግዚአብሔር ተራራ እስከ ኮሬብ ድረስ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ሄደ። እዚያም ወዳለ ዋሻ መጣ፥ በዚያም አደረ እነሆም። ኤልያስ ሆይ፥ በዚህ ምን ታደርጋለህ? የሚል የእግዚአብሔር ቃል ወደ እርሱ መጣ። እርሱም፦ ለሠራዊት አምላክ ለእግዚአብሔር እጅግ ቀንቻለሁ የእስራኤል ልጆች ቃል ኪዳንህን ትተዋልና፥ መሠዊያዎችህንም አፍርሰዋልና፥ ነቢያትህንም በሰይፍ ገድለዋልና እኔም ብቻዬን ቀርቻለሁ ነፍሴንም ሊወስዱአት ይሻሉ አለ። እርሱም፦ ውጣ፥ በተራራውም ላይ በእግዚአብሔር ፊት ቁም አለ። እነሆም፥ እግዚአብሔር አለፈ፥ በእግዚአብሔርም ፊት ትልቅና ብርቱ ነፋስ ተራሮቹን ሰነጠቀ ዓለቶቹንም ሰባበረ፥ እግዚአብሔር ግን በነፋሱ ውስጥ አልነበረም። ከነፋሱም በኋላ የምድር መናወጥ ሆነ፥ እግዚአብሔር ግን በምድር መናወጥ ውስጥ አልነበረም። ከምድር መናወጥ በኋላ እሳት ሆነ፥ እግዚአብሔር ግን በእሳቱ ውስጥ አልነበረም። ከእሳቱም በኋላ ትንሽ የዝምታ ድምፅ ሆነ። ኤልያስም ያን በሰማ ጊዜ ፊቱን በመጐናጸፊያው ሸፈነ፥ ወጥቶም በዋሻው ደጃፍ ቆመ። እነሆ። ኤልያስ ሆይ፥ በዚህ ምን ታደርጋለህ? የሚል ድምፅ ወደ እርሱ መጣ። እርሱም፦ ለሠራዊት አምላክ ለእግዚአብሔር እጅግ ቀንቻለሁ የእስራኤል ልጆች ቃል ኪዳንህን ትተዋልና፥ መሠዊያዎችህንም አፍርሰዋልና፥ ነቢያትህንም በሰይፍ ገድለዋልና እኔም ብቻዬን ቀርቻለሁ ነፍሴንም ሊወስዱአት ይሻሉ አለ። እግዚአብሔርም አለው፦ ሂድ፥ በመጣህበትም መንገድ በምድረ በዳ ወደ ደማስቆ ተመለስ ከዚያም በደረስህ ጊዜ በሶርያ ላይ ንጉሥ ይሆን ዘንድ አዛሄልን ቅባው በእስራኤልም ላይ ንጉሥ ይሆን ዘንድ የናሜሲን ልጅ ኢዩን ቅባው በፋንታህም ነቢይ ይሆን ዘንድ የአቤልምሖላን ሰው የሣፋጥን ልጅ ኤልሳዕን ቅባው ከአዛሄልም ሰይፍ ያመለጠውን ሁሉ። ኢዩ ይገድለዋል ከኢዩም ሰይፍ ያመለጠውን ሁሉ ኤልሳዕ ይገድለዋል። እኔም ከእስራኤል ጕልበታቸውን ለበኣል ያላንበረከኩትን ሁሉ፥ በአፋቸውም ያልሳሙትን ሁሉ፥ ሰባት ሺህ ሰዎች ለእኔ አስቀራለሁ።; *1ኛ ነገ 19፡4-15፡፡*

# ኤልያስ - 1ኛ ነገሥት 18

## *ድፍረት*

- #ኤልያስም። እስራኤልን የምትገለባብጡ፥ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትታችሁ በኣሊምን የተከተላችሁ፥ አንተና የአባትህ ቤት ናችሁ እንጂ እኔ አይደለሁም። ኤልያስም ወደ ሕዝቡ ሁሉ ቀርቦ። እስከ መቼ ድረስ በሁለት አሳብ ታነክሳላችሁ? እግዚአብሔር አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ በኣል ግን አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ አለ። ሕዝቡም አንዲት ቃል አልመለሱለትም።; *1ኛ ነገ 18፡18 እና 18፡21።*

## *መገዳደር፡- 1ኛ ነገ 18፡23-24*

- #አሁንም ልከህ እስራኤልን ሁሉ፥ በኤልዛቤልም ማዕድ የሚበሉትን አራት መቶ አምሳ የበኣልን ነቢያት፥ አራት መቶም የማምለኪያ ዐፀድን ነቢያት ወደ እኔ ወደ ቀርሜሎስ ተራራ ሰብስብ አለ። ሁለት ወይፈኖች ይሰጡን እነርሱም አንድ ወይፈን ይምረጡ፥ እየብልቱም ይቍረጡት፥ በእንጨትም ላይ ያኑሩት፥ በበታቹም እሳት አይጨምሩ እኔም ሁለተኛውን ወይፈን አዘጋጃለሁ፥ በእንጨቱም ላይ አኖረዋለሁ፥ በበታቹም እሳት አልጨምርም። እናንተም የአምላካችሁን ስም ጥሩ፥ እኔም የእግዚአብሔርን ስም እጠራለሁ ሰምቶም በእሳት የሚመልስ አምላክ፥ እርሱ አምላክ ይሁን፦ ሕዝቡም ሁሉ። ይህ ነገር መልካም ነው ብለው መለሱ። ;

## *ለጸሎት የተሰጠ መልስ*

- #የእግዚአብሔርም እሳት ወደቀች፥ የሚቃጠለውን መሥዋዕቱንም እንጨቱንም ድንጋዮቹንም አፈሩንም በላች፥ በጕድጓዱም ውስጥ ያለውን ውኃ ላሰች።; *1ኛ ነገ 18፡38*

## *ንስሐ፡- 1ኛ ነገ 18፡39*

- #ሕዝቡም ሁሉ ያንን ባዩ ጊዜ በግምባራቸው ተደፍተው። እግዚአብሔር እርሱ አምላክ ነው አሉ።;

## *በዲያቢሎስ ላይ የተገኘ ድል*

- #ኤልያስም። ከበኣል ነቢያት አንድ ሰው እንዳያመልጥ ያዙ አላቸው። ያዙአቸውም ኤልያስም ወደ ቂሶን ወንዝ ወስዶ በዚያ አሳረዳቸው።; *1ኛ ነገ 18፡40*

# ኤልያስ - 1ኛ ነገሥት 18

*ግምት*

- የእስራኤል ልጆች ቃልኪዳንህን ረሱ፤ መሠዊያውንም ሰባበሩ፤ ነቢያትህንም በሰይፍ ገደሉ፤ እኔ ብቻ ቀርቻለሁ እኔንም ነፍስ ሊወስዷት - ሊገድሉኝ ይሻሉ።

*እውነታው*

- ሕዝቡም ሁሉ ያንን ባዩ ጊዜ በግምባራቸው ተደፍተው። እግዚአብሔር እርሱ አምላክ ነው አሉ። *1ኛ ነገ 18፡39*

- … የእግዚአብሔርም እሳት ወደቀች፥ የሚቃጠለውን መሥዋዕቱንም እንጨቱንም ድንጋዮቹንም አፈሩንም በላች፥ በጕድጓዱም ውስጥ ያለውን ውኃ ላሰች። *1ኛ ነገ 18፡39*

- ኤልያስም። ከበኣል ነቢያት አንድ ሰው እንዳያመልጥ ያዙ አላቸው። ያዙአቸውም ኤልያስም ወደ ቂሶን ወንዝ ወስዶ በዚያ አሳረዳቸው። *1ኛ ነገ 18፡40*

*ኤልያስን ወደ መታወክ እንዲገባ ያደረገው ምንድር ነው?*

- ታላቅ ስኬቱን ተከትሎ የነበረ ጫና፤ ኩራት፤ ስሜት አሊያም ነገሮችን በቅደም ተከተል ማሰብ?

# መፍትሔዎች

1. *በእውነታው ላይ ጥልቅ ትኩረት እናድርግ*
   - *ኤልያስ በፍርሐቱ፣ በውድቀቱ… ላይ ትኩረት አደረገ*
   - *በራሳችን ክንዋኔ ሳይሆን በእግዚአብሔር ኃይል… እንታመን*

## ዘወትር ስሜታችንን የምናምን ሆነን አንገኝ

## አንዳንድ ጊዜ ክፍተቶች እንዲገጥሙን እንፍቀድ - ሰዎች ነንና!!!

## ስሜታችንን እንግለጽ ቢሆንም በስሜቶታችን አንመንባቸው።

2. ራሳችንን ከሌሎች ጋር አናወዳድር

3. ሚዛናዊነት የጎደላቸውን ወቀሳዎችን ንቀን እንተዋቸው

4. የገጠሙንን ያልጠበቅናቸው ጉዳዮች ማጋነንን እንተው

# በዚህ ሁኔታ ውስጥ እግዚአብሔር እንዴት ይረዳናል?

1. ለሰውነታችን ፍላጎት ይጠነቀቅልናል
   - አይወቅሰንም
   - #ተነስተን እንድንመገብ; ያደርገናል
   - እንደ ደቀመዛሙርቱ ይከባከበናል። ዮሐ 16፡16-23።
2. ችግራችንን ሁሉ ወደ ርሱ እንድናቀርብ በመሻት
   - ፍርሐታችንን፤ ተስፋ መቁረጣችንን፤ ብቸኝነታችንን፤ ሰላም ማጣታችንን፤ በአንዳንድ ነገር መሸማቀቃችንን፤ …
3. እግዚአብሔርን የተሳሳተውን ትተን በትክለኛ መንገድ ስናውቀው

   #እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።; ሮሜ 8፡28
   #በሰው ዘንድ የማይቻል በእግዚአብሔር ዘንድ ይቻላል።; ሉቃስ 18፡27
   #እነሆ፥ የእግዚአብሔር ዓይኖች ወደሚፈሩት ናቸው፥ በምሕረቱም ወደሚታመኑ።; መዝ 33፡18
   #የድሀውን ልቅሶ ወደ እርሱ ያደርሱ ዘንድ፥እርሱም የችግረኛውን ድምፅ ይሰማ ዘንድ፥እርሱን ከመከተል ፈቀቅ ብለዋልና፥ከመንገዱም ሁሉ አንዱን አልተመለከቱምና።; ኢዮብ 34፡28
4. በሕይወታችን ትክክለኛ አቅጣጫ ስንይዝ

   #እግዚአብሔርም አለው፦ ሂድ፥ በመጣህበትም መንገድ በምድረ በዳ ወደ ደማስቆ ተመለስ ከዚያም በደረስህ ጊዜ በሶርያ ላይ ንጉሥ ይሆን ዘንድ አዛሄልን ቅባው በእስራኤልም ላይ ንጉሥ ይሆን ዘንድ የናሜሲን ልጅ ኢዩን ቅባው በፋንታህም ነቢይ ይሆን ዘንድ የአቤልምሖላን ሰው የሣፋጥን ልጅ ኤልሳዕን ቅባው ከአዛሄልም ሰይፍ ያመለጠውን ሁሉ። ኢዩ ይገድለዋል ከኢዩም ሰይፍ ያመለጠውን ሁሉ ኤልሳዕ ይገድለዋል። እኔም ከእስራኤል ጕልበታቸውን ለበኣል ያላንበረከኩትን ሁሉ፥ በአፋቸውም ያልሳሙትን ሁሉ፥ ሰባት ሺህ ሰዎች ለእኔ አስቀራለሁ።; 1ኛ ነገ 19፡15-18

5. ያለዋጋ በነጻ በሚያክሙን መንፈሳውያን አባቶች - መምህረ ንስሐ

# ማጠቃለያ

*<u>በነቢዩ ኤልያስ</u>*

- በ1ኛ ነገሥት ምዕራፍ 18 እና ምዕራፍ 19 እንደምናነበው ንግሥት ኤልዛቤል በነቢዩ ኤልያስ የተነሳ በምድራቸው ረሐብ ስለሆነ እጅግ ተበሳጭታ ነበር።

- ኤልዛቤል በዚሁ የተነሳ ንግግርዋ ሁሉ ያልታረመና ነውረኛ ነበር። ኤልያስንም ማግኘት ስላልቻለች የእግዚአብሔርን ነቢያት መግደል ጀመረች።

- ኤልዛቤል አልያስን ማግኘት ስላልቻለች ወዳጆቹን ማጥቃት ጀመረች።

- በዚህ ጊዜ ኤልያስ ታወከ፤ የሚከተሉትም አምስት ነገሮች ታዩበት። እነዚህም ለሕይወት ቀውስ መከሰት ምልክቶች ናቸው። አነዚህም ምልክቶች፦
    1. ክስተቱ ከታላቅ አገልግሎት ውጤት በኋላ የተፈጠረ ነበር። ይህም ብዙ ቀውሶች በበጎ ሥራችን ያፈራነው መልካም ውጤቶችን ተከትለው መምጣታቸውን የሚያሳይ ነው።
    2. ከግኑኝነት መቋረጥ በኋላ መከሰቱ። ከአለቃችን፤ ከእጮኛ፤ ከትዳር ጓደኛ ጋር ያለን ግኑኝነት ሲሻክር መደበት ይከሰታል።
    3. ከፍተኛ የድካም ስሜት ሲሰማን ይህን ተከትሎ ይፈጠራል። ኤልያስ 450 ሐሰተኛ ነቢያትን ከጨረሰ፤ ዝናብ እንዲዘንብ በርትቶ ከጸለየ፤ በእግዚአብሔር ኃይል ረጅም መንገድ ከተጓዘ በኋላ አልደከመውም ይሆን? በሁሉ ሊያምርልን አይቻልም። የምንችለውን ካላደረግን በየዕለቱ ከሚሰማንና ከአቅም በላይም ከምንሞክረው ከበድ ያለ ነገር የተነሳ ቀውስ ይገጥመናል።

# የሕይወት ቀውስ …

4. ታላቅ ድልን ተከትሎ ይፈጠራል። ተማሪዎች ዲፕሎማቸውን ይዘው ለምን ይጨነቃሉ? እናቶች ጤነኛ ልጅ ታቅፈው ስለምን ይታወካሉ?
5. ያልጠበቅነው ታላቅ ተስፋ አስቆራጭ ነገር ከተከሰተ በኋላ። ኤልያስ ከሆኑት ሁኔታዎች ሁሉ በኋላ አክአብና አልዛቤል ንስሐ ገብተው ከእግዚአብሔር ምሕረትን የለምናሉ ብሎ አስቦ ነበር። ነገር ግን የሆነው ይህ ሳይሆን ኤልዛቤል የበለጠ ተበሳጭታ አልያስን ለመግደል መፈለጓ ነበር።

ይህም በሚከተሉት ሦስት ቀላል መንገዶች ወደ ቀውስ ውስጥ ይከተናል።

1. የራሳችን የምንለው ቦታ እንፈልጋለን። ኤልያስም ረጅም መንገድ እንደሄደ።
2. የአንድን ጉዳይ መጥፎ ገጽታ ብቻ መመልከት።
3. የእግዚአብሔርን ስጦታ መርሳት።

<u>የማጠቃለያ መፍትሔዎች፡ 2ኛ ነገሥት ምዕራፍ 2</u>

1. እግዚአብሔር እንዲረዳን ፈቃደኛ መሆን
2. የእግዚአብሔርን ስጦታ መቀበል
3. እግዚአብሔር ያለንን ወዲያው መፈጸም
4. ከሰዎች ጋር እንሁን። እግዚአብሔር ለኤልያስ ኤልሳዕን እንዳዘጋጀ ይሰጠናልና
5. በሌሎች ሰዎች ችግር ላይ አትኩሮት ማድረግ። ይህም የራሳችንን እንድንረሳ ያደርገናል። #እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት፥ ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ።; <u>*ፊል 2፡4።*</u>

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

ይቆየን።